# ፀረ-ኢሕአፓ ጥላ -ወጊ እንቅስቃሴና ከይሲ ፖለቲካ፣ምንም ሳይፈይድ እንደ እሾህ ማገዶ ተንጣጥቶ አመድ በመሆን መድረሻው ቤተ መንግሥት ሳይሆን ሲያል ነው ።

ከአስተዋይ በቀለ

ስማ አንተ ሐቀኛ አይበገሬ ታጋይ !

በዚህ ቀውጢና ወሳኝ ወቅት፣ ብቸኛ አለኝታችን፣ ብርታታችንና ኃይላችን ሆኖ የተገኘው ሐቀኛ ሕዝባዊ ድርጅት አንድ ለእናቱ ለኢትዮጵያ የሆነው ኢሕአፓ ብቻ ነው።

አንድ አገር፣ አንድ ሕዝብ፣ አንድ ሰንደቅ ዓላማ፣አንድ ኢሕአፓ እንጂ ሌላ የለም። አለ የሚል ካለ፣የወያኔን አለዚያም የግንቦት 7ን መታወቂያ በምስጢር በኪሱ የሸጐጠና ባልበረደ አድርባይነትና መረን በለቀቀ የሥልጣን ጥም በከንቱ የሚኳትን አፋዳሽ  ወይንም ደግሞ በአፍሪካ ቀንድ የኢሉሚናቲ ግቦች አስፈፃሚ የሆነ ቅጥረኛ መሆን አለበት።

ልብ በል በውል !

አገርና ሕዝብን በክፉ ቀን የሚመለከት ሙያ በልብ ነው እንጂ እንደ ግንቦት 7 ካርታ ላይ በሌለ አውድማ በባዶ ቤት ፊሽካ መንፋትና  በኢሳት መቦጥረቅ ወይም እንደ ግብዛን ፈሪሳዊያን ጥሩምባ እያስነፉ መመፃደቅ ወይንም ደግሞ በየሲፖዚየሙና በየቀዳዳው ማምቦራጨቅና ቱልቱላ መንፋት አይደለም።

ኢሕአፓ በኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ሆኖ ብሔራዊ አመፅ በምስጢር እያቀጣጠለ የሚገኝ ሲሆን፣ ነገ ጠላቶቹ በመገረምና በመደነቅ ዓይናቸውን አፍጥጠው የሚያዩት የድል ባለቤት ነው። ለዚህ ለማይቀረው ድል አድራጊነቱ ጥላ- ወጊ ሆኖ መገኘት በቀጥታ ከወያኔ ጋር የሚያሰልፍ በአገርና በሕዝብ ጥቅም ላይ የተፈፀመ ከፍተኛ ትሪዝን ሆኖ ይቆጠራል።

ስለዚህ ይህ ሳይገባው ወይንም እያወቀ ሆን ብሎ ማንም በፀረ- ኢሕአፓ አቋም ቢንጨረጨርና ቢልመሰመስ፣ ውጤቱ እንደ እሾህ ማገዶ ተንጣጥቶ በመክሰል አንድና አንድ ብቻ በሆነው ኢሕአፓ ጫማ ሥር አመድ ሆኖ መቅረት ይሆናል እንጂ ፈፅሞ የሚፈይደው የለውም።

ጊዜው፣ ምሪቱና ድል ለኢሕአፓና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ! ! !